# በቶሮንቶ የቅንጅት ደጋፊዋችና አባላት

ለቅንጅት የኢትዮጵያ የባህልና የእርዳታ ድርጅት: ቶሮንቶ

ቀን 12/12/2006

ከግንቦት 2006 ጀምሮ የቶሮንቶ የቅንጅት ድጋፍ እንቅስቃሴ እየተዳከመ ባለበት ወቅት አመራሩ ደጋፊውንም ይሁን አባላቱን ሳያማክርና ሳያወያይ ህዝብ ሊከፋፍል የሚችል ወገናዊ የሆነ የቸኮለ እርምጃ መወሰዱ ስላሳዘነንና በዚሁም ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ከአንዴም ሁልቴ ቀጠሮዎች ከያዝን በሁአላ በመጨረሻው ያለብቂ ምክንያት ቀጠሮዎች በመሰረዛቸውና ለማነጋገርም ፈቃደኛ ባለመሆናችሁ ሽማግሌዎች ልከን በኖቬምበር 17 2006 ከአምስት ሰአት በላይ የፈጀ ውይይት ማድረጋችን ይታወሳል

ባቀረብነውም ደብዳቤ የታሰሩ የቅንጅት መሪዎቻችንን በአስቸኩአይ ለማስፈታትና እስከዝያውም ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት በኢትዮጵያችንም የዲሞክራሲን ግንባታ ከግቡ ለማድረስ በቶሮንቶ ከተማ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን አበይት ጉዳዮች አንስተን ተወያይተናል::

1. በአባላትነትም ይሁን በደጋፊነት ከናንተ ጋር ለብዙ ጊዜ መቆየታችንና የጉዳዩ ባለቤት በመሆን በሙሉ እምነትና ልብ ስንሳተፍ መቆየታችንን
2. ሙሉ ሃይላችንን በወቅቱ አንገብጋቢ ለነበረው ምርጫ 97 እና ከዝያም በሁአላ በምርጫው ማግስት ተከትሎ የመጣውን የዲሞክራሲን ቅልበሳንና የመሪዎቻችን መታሰር ጉዳይ ላይ ማዋላችንን
3. ይህም ሆኖ በየግዜው በቶሮንቶ ጽ/ቤት በኩል ይታዩ የነበሩትን ድክመቶች(በደብዳቤያችን ላይ ያሉትን ጨምሮ) ለማረምና አመርቂ ስራ ለመስራት የቶሮንቶ ቅንጅት እንደ ኢትዮጵያው ቅንጅት ተቀርጾ እንደ ህዝብ ትግልነቱ የህዝብን ተሳትፎ ያካተተ በግልጽነት፤ በተጠያቂነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መደራጀት እንዳለበት ጥያቄ ማቅረባችንን
4. ለነዚህም ጥያቄዎቻችን በመጨረሻ የተሰጠን  መልስ አሁን ያለው የቅንጅት የድጋፍ ጽ/ቤት ከአዲስ አበባ በቀጥታ በተሰጠው መመርያ የተደራጀና የመተዳደርያ ደንብም እንዳለው በመጥቀስ ማንኛውም አባልም ሆነ ደጋፊ በዚሁ መመርያ ብቻ ተሳትፎ ሊያደርግ እንደሚችልና በቦርድ ውስጥ ለመመረጥም በጽ/በቱ ስራ አስኪያጆች ብቻ እንደሚወሰን ገልጻችሁልን አንድ ኮፒ የድርጅቱ ነው ያላችሁትን ደንብ እንድንነጋገርበትና አስተያየት እንድሰጥበት ሰጥታችሁን ነበር::

እኛም የመተዳደርያ ደንቡን ከተመለከትን በሁአላ የሚከተለው ተገንዝበናል::
በመተዳደርያ ደንቡ በገጽ 1 መግብያ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጣችሁት ለብዙ ግዜ የመላው አማራ ህዝብ የድጋፍ ድርጅት ሆናችሁ ስትሰሩ ከቆያችሁ በሁአላ የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት ወደ መላው ኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ድርጅት ሲለወጥ እናንተም ይህንኑ ተከትላችሁ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ድጋፍ አካል መሆናችሁና በጥቅምት 1997 መኢአድ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሲቀናጅና: ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሲመሰረት እናንተም የድጋፍ ድርጅቱን በማስተካከል ድጋፍ የመስጠት ተግባራችሁን እንደቀጠላችሁ ያስረዳል::
ከላይ እንደተገለጸው በየደረጃው ከመ.አ.ህ.ድ. ወደ መ.ኢ..አ.ድ. ከዚያም ወደ ቅንጅት ስትለወጡ የስም ለውጥ እያደርጋችሁ ቀጠላችሁ እንጂ አንድ ዲሞክራስያዊ ድርጅት ማድረግ እንደሚገባው አባላቶቻችሁንና ደጋፊዎችን አወያይታችሁ ያጸደቃችሁት መተዳደርያ ደንብ እንዳልሆነ ያስረዳል::

ይህንንም ሙሉ ለሙሉ ለማለት ያስደፈርን በተለይ ቅንጅት ከመመስረቱ ቢያንስ ስድስት ወራት አስቀድሞ በጽ/በቱ በአባልነትና በደጋፊነት እንሳተፍ ስለነበር; አንድም ጊዜ የመተዳደርያ ደንብ ረቆ ለውይይት ቀርቦ እንዳልጸደቀ ስለምናውቅ ነው:: በዚህም መሰረት ይህ ያቀርባችሁልን መተዳደርያ ደንብ ቅንጅትን አፍቃሪ ድጋፊዎች በተለይም አባላት ያልመከሩበትና ያላጸደቁት መቼና በማን እንደረቀቀና፣ እንደጸደቀ በቅጡ ያላስቀመጠ የቅንጅትንም ማኒፈስቶ የተከተለ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም::

ጊዜው የሚጠይቀውን ከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎ ለማግኘት ሁሉንም በማሳተፍ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልክ አሰራራችንን በዲሞክራስያዊ መልክ ባደረግን ቁጥር በር የተዘጋባቸውና እውቀታቸውንና ችሎታቸውን ለትግላችንን አስትዋጽዎ ለማድረግ እየፈለጉ በጽ/በቱ በኩል በሚደርግባቸው የማግለል አሰራር ምክንያት  የማይሳተፉ ኢትዮጵያውያን ወደ ትግሉ እንደሚመጡ እርግጠኞች ነን::

በመሆኑም ሁሉም አባልም ሆነ ደጋፊ በነጻነት መክሮበትና አምኖበት የሚያጸድቀው መተዳደርያ ደንብ ስለሚያስፈልግ ከኛ ከቅሬታ አቅራቢዎች አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ከጽ/በቱ ቦርድ አባላት የተውጣጣ ጊዝያዊ ኮሚቴ ተሰይሞ ረቂቅ ደንብ ካተዘጋጀ በሃላ በቶሮንቶ ከተማና አካባቢው የሚገኙ ደጋፊና አባላቶችን ስብሰባ ጠርቶ በማወያየት አዲስ የመተዳደርያ ደንብ እንዲጸድቅ እና የአመራር አባላትም ምርጫ እንዲካሄድ እንጠይቃለን:: ለዚህም ጥያቄያችን እስከ ዲሰምበር 20 2006 ምላሽ እንድትሰጡን እናሳስባለን

በመጨረሻም: በሽማግሌነት ተልካችሁ ላወያያችሁንና ለችግሮቻችን መፍትሄ ለመሻት ለደከማችሁት አባቶቻችን ወንድሞቻችንና እህቶችን የከበረ ምስጋናችንን እናቀርብለን

ለአንድ ቅንጅት በጋራ እንታገል
ቅንጅት የህዝብ ትግል ነው:: ግልጽነት፣ አንድነትና፣ ዲሞክራስያዊነት የቅንጅት መንፈስ ነው
በቶሮንቶ የቅንጅት ደጋፊዋችና አባላት

kinijittoronto@gmail.com